# ትግሉን ከማፋፋም ውጪ ሌላ አማራጭ የለም።
# በወቅቱ ሁኔታ ላይ ከኦነግ የቀረበ ጥሪ

የአንገዛም ባይነት ፀረ ወያኔ ትግል በተለያየ መልኩ እየተፋፋመ ባለበት ባሁኑ ወቅት የኦሮሞ ህዝብ ፍላጎቱን የሚያሟላበትን ትግል ከማፋፋም ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለው እናስገነዝባለን

የወያኔ አናሳ መንግሥት ላለፉት አስራ አራት አመታት በኦሮሞ ህዝብና በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ላይ እጅግ በጣም ዘግናኝ ጭቆናና አፈና ሲያደርስ ቆይቷል። ህዝቦችም መብታቸውን ለመጎናጸፍ ያልታቋረጠ ትግል ሲያካሄዱ ቆይተዋል። በዚህ ትግል ውስጥም ከፍተኛ መስዋእትነት ተከፍሏል።በልጆቹ ቆራጥ ተጋድሎና መስዋእትነት የተቀጣጠለው የኦሮሞ ህዝብ የአልገዛም ባይነት ፀረ ጭቆና ትግልም በመላ ኢትዮጵያ

ውስጥ ተፋፍሞ አገሪቷን እያመሰ ነው።

በመሆኑም የኦሮሞ ህዝብ መሰረታዊ አላማው ላይ በመመርኮዝ ትግሉን በቆራጥነት በወያኔ መንግስት ላይ በማነጣጠር ያልገዛም ባይነት አመፁን በሁሉም መስክ ማካሄድ ይጠበቅበታል። ላገሪቷና ለአካባቢው ማነቆ ከሆነው የፖለቲካ ችግር ለመላቀቅና በአሸናፊነት ለመውጣት የኦሮሞ ህዝብ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ሁሉ በመክፈል ወሳኝ ሃይል ሆኖ መውጣት ያለበት ወቅት አሁን ነው።

በዚህ ወሳኝ ወቅት ማቅማማትና ትግልን ከማፋፋም መቆጠብ ከኦሮሞ ህዝብ አይጠበቅም። ወያኔ ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ሰላም መንግሥት ነው። የወያኔ መንግሥት ፍላጎትና አላማ የኦሮሞን ህዝብ በማታለልና በማባበል ለነፃነቱና ለመብቱ የሚያደርገውን ትግል ማኮላሸት ነው። የወያኔ አናሳ መንግሥት ሰላምን ለማስገኘት ፈፅሞ ዝግጁ አይደለም። ትግልን አጠናክሮ መቀጠል ብቻ ነው እውነተኛና አስተማማኝ ሰላም ሊያስገኝ የሚችለው። በመሆኑም የኦሮሞ ህዝብ ባፋጣኝ ካለመው ግብ ለመድረስ ትግሉን ከማጠናከር ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለው አበክረን እናስገነዝባለን።

ወያኔ የሚናገረውና የሚተገብረው ለየቅል መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። ወያኔ እያናፈሰ ያለው የሰላም ውይይትም ሀቀኛ ውይይት ሳይሆን የህወሐትን የበላይነት የሚያረጋግጥና የሥርአቱን እድሜ የሚያራዝምለትን ውይይት ብቻ ነው የሚሻው። የኦሮሞን ህዝብ በሚነዛው የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ሊያታልለው የሚሞክረውም ጊዜ ሊሸምትበትና የዝቡን ስነልቦና በመስለብ ከትግሉ እንዲዘናጋ ለማድረግ እንጂ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ መፍትሄ እንዲያገኝ ለማስቻል እንዳልሆነ እሙን ነው። ስለሆነም የኦሮሞ ህዝብና ታጋዮች የዚህ ሃሰት ፕሮፓጋንዳ ሰለባ መሆን የለባቸውም እንላለን።

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የኦሮሞ ህዝብ ወሳኝ ሚና እንዳለው የሚረጋገጥበት ወቅት አሁን ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ ያለው ብቸኛ አማራጭ በመላው አገሪቷ ውስጥ በመቀጣጠል ላይ የሚገኘውን ህዝባዊ አመፅ በማጧጧፍ አጠቃላይ መፍትሄና አስተማማኝ ሰላም እንዲያስገኝ ማስቻል ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ የኦነግ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎችንና ጥሪዎችን ያስተላልፋል።

1. የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት የወቅቱን ሁኔታ እንዲቆጣጠርና ትግሉን

ADDA BILISUMMAA OROMOO
O.L.F.
OROMO LIBERATION FRONT

ይበልጥ እንዲያፋፍም ለማስቻል የኦሮሞ ህዝብ በሙሉ ከኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት ጎን እንዲሰለፍ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

2. የኦሮሞ ህዝብ ህፃን አዋቂ ሳይል በሁሉም አካባቢ በአንድነት በመነሳትና በተለያዩ ስልቶች በመጠቀም አካባቢውን እንዲቆጣጠር

3. አውቀውም ሆነ ባለማወቅ የኦሮሞን ህዝብ ለቁም ስቃይ ካጋለጠው መንግሥት ጋር የወገኑ የኦሮሞ ተወላጆች በሙሉ ወቅቱ ባስገኘላቸው እድል በመጠቀም የህዝባችንን ትግል በመደገፍ ካለፈው ስተታቸው ራሳቸውን እንዲያፀዱ አነግ ጥሪውን ያስተላልፋል።

4. ጭቁን ብሄሮችና ህዝቦች እንዲሁም ዲሞክራሲን እውን ለማድረግ በመታገል ላይ ያሉ ሀይሎች በሙሉ በመካሄድ ላይ የሚገኘውን ፀረ አምባገነናዊ አገዛዝ ትግል እጅ ለእጅ ተያይዘው ይበልጥ እንዲያፋፍሙ አነግ ጥሪውን ያቀርባል።

5. የወያኔ መንግሥት ላለው የፖለቲካ ችግር በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ ከማፈላለግ በሃይል ለማፈን በመምረጡ ላለፉት አሥራ አራት አመታት አገሪቷንና ህዝቦችን ሰላም ነስቷል። በነዚህ አመታት ውስጥ ለደረሱትና እየደረሱ ላሉት ጭፍጨፋዎችም ተጠያቂው ፀረ ህዝብ የሆነው የወያኔ መንግስት በመሆኑ የዚህ ሥርአት ደጋፊዎች ስርአቱን ከመደገፍ እንዲቆጠቡና ከህዝቦች ትግል ጎራ እንዲሰለፉ አነግ ይጠይቃል።

6. በኦሮሞ ሲዳማ አኙዋክ ሶማሌ አማራ ሸኮመዠንገርና በሌሎች ህዝቦች ላይ ለደረሰውና እየደረሰ ያለውን የህይወትና የንብረት ጥፋት በማጣራት ለፍትህ የሚያቀርብ ከወያኔ መንግሥት ቁጥጥር ነፃ የሆነ ያጣሪ ኮሚሽን ባፋጣኝ እንዲቋቋም

7. ሃገሪቷን እያመሰ ላለው የፖለቲካ ችግር አስተማማኝ መፍትሄ ሊገኝ የሚችለው ወያኔ ኢህአደግን ጨምሮ ሁሉንም ፓርቲዎች ያካተተ ሁለ ገብ ኮንፍረንስ ሲካሄድ ብቻ በመሆኑ ሃገሪቷን ከጥፋት ለማዳን የሚሹ ሁሉ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሰሩ አነግ ይጠይቃል።

8. ከአለም ህብረተሰብ በሚያገኘው የገንዘብና የዲፕሎማሲ ድጋፍ የአን ባገነንነት አገዛዙን መቀጠል የወያኔ መንግሥት ፍላጎት ነው። በመሆኑም የአለም ህብረተሰብ ባገሪቷ ላይ የሚከተሉን ፖሊሲ መልሰው በመገምገም ሀገሪቷ የባሰ ችግር ውስጥ ከመዘፈቋ በፊት አጠቃላይ መፍትሄ በማስገኘት ላይ እንዲያተኩሩ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጥሪውን ያስተላልፋል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ**
**የኦሮሞ ነፃነት ግንባር**

**ህዳር** 2005